የወ/መ/ቁጥር 160651

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ ፍቅረማርያም ታደሰ እንዳለ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተሻሻለ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በቀጥታ በመናገር ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8፣30 ሰዓት ሲሆን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/08 ልዩ ቦታው ከፍተኛ ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ የግል ተበዳይ አቶ ቢተው ዳዊትን እናትህ ትበዳ፤ አንተ ቆማጣ፤ ሸባ፤ ሙጀሊያም ብሎ በመናገሩ በፈፀመው የስድብና ማዋረድ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳዩን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹም በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ እዚህ ፍ/ቤት ግቢ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መረጃ ክፍል አካባቢ በክሱ ላይ በተመለከተው ሁኔታ ተከሳሽ የግል ተበዳይን በመናገር የማዋረድና የስድብ ድርጊቱን የፈፀሙበት መሆኑን በግልፅ አስረድተዋል። በመሆኑም ተከሳሽ በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብለው ሁለት የመከላከያ ምስክሮች በማቅረብ ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገቡት ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ.ም ተከሳሽ ከቀኑ 6፣00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 10፣00 ሰዓት ድረስ ሀዘን ቤት የነበሩ መሆኑን እናስረዳለን፤ ይሄውም የተከሳሽ ጓደኛ አቶ ናርዶስ አበበ አጎታቸው አቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴ አርፈው እዚያ ሀዘን ተቀምጠው እያለ ለመድረስ በቦታው የተገኙ መሆኑን እናስረዳለን የሚለውን ሲሆን በዚሁ መሰረት የመከላከያ ምስክሮቹም መታላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። ከዚህ በተጨማሪም ተከሳሽ ድርጊቱን የፈፀሙት እዚሁ ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ መጥሪያ ክፍል አካባቢ ስነበርና በቦታው የፍ/ቤት ሰራተኞች ስለነበሩ ቀርበው በተጨማሪ ምስክርነት ይሰሙልኝ በማለት ዐ/ሕግ ባመለከተው መሰረት ሦስት ምስክሮች ቀርበው ተሰምተዋል፤ ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ተከሳሽ ጓደኛቸው መሆኑን ገልፀው ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በሀዘን ምክንያት እንጦጦ አካባቢ ከቀኑ 6፡00 ሰዓት እስከ 10፡00 ሰዓት አካባቢ ድረስ አብረን ነበርን በማለት አስረድተዋል። ይህም ደግሞ ተከሳሽ ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለው ቦታ አልነበሩም የሚለውን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ ተከሳሽና የግል ተበዳይ እዚህ ፍ/ቤት ግቢ ካለው የባለጉዳዮች ማስተናገጃ ከሆነው የመረጃ ዴስክ አካባቢ በክሱ ላይ በተመለከተው ቀንና ሰዓት ሲጨቃጨቁ እንደነበር ለግራቀኙ(ተከሳሽና የግል ተበዳይ) ይወግናሉ ተብለው የማይገመቱት የፍ/ቤቱ ሰራተኞች አስረድተዋል። ይህ ከሆነ ደግሞ ተከሳሽ ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ አልነበርኩም፤ ካልነበርኩ ደግሞ ድርጊቱን ፈፅመሀል ልባል አልችልም በማለት ያቀረቡት ክርክር መሰረት የሌለውና ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻሉ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ ስለ ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ.ም የወንጀል ድርጊት የቅጣት ማክበጃ አለን ይሄውም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (ሠ) መሰረት ተከሳሹ ድርጊቱን የፈፀሙት አካል ጉዳተኛ በሆነው የግል ተበዳይ ላይ ስለሆነ ነው ብለዋል። የወንጀል ደረጃው ሲወሰንም ከባድ ተብሎ እንዲወሰን ምክንያቱም ድርጊቱ የተፈፀመው በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ስለሆነና የስድቡ አይነትም ሞራልን የሚነካ በመሆኑ ነው አሉ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 34 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ ዲፕሎማ ነው፤ ትደርና ልጅ የለኝም፤ የምረዳቸው እህትና ወንድሞች እንዲሁም ደካማ አባት አለኝ እነሱን እረዳለሁ፤ የወር ገቢዬ ብር 1990.00(አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ብር) ነው፤ አሁን የምሰራው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሂሳብ ሹምነት ነው፤ ድርጊቱ ተፈፀሚል ከተባለ ተከሳሽና የግል ተበዳይ የቦታ ክርክርን መሰረት አድርጎ በርካታ ክሶች ያሉን ሲሆን፤ የግል ተበዳይ በተከሳሽ ይዞታ ውስጥ እየኖሩ በፍ/ቤት ተከሰው ተፈርዶባቸው ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ላይ ይገኛል፤ ተከሳሽ በስራ ክርክር ምክንያት ሲከራከሩ ቆይተው ተፈርዶላቸው አሁን ገና ነው ሥራ የጀመሩት፤ የመ/ቤታቸውን የሰራተኞች ደመወዝ ለማሻሻል በመስራት ላይ ናቸው፤ በመሆኑም ቅጣቱ በገንዘብ እንዲሆንልኝ፤ ይህ ካልሆነ ቅጣቱ እንዲገደብልን በማለት ከጠበቃቸው ጋር በመሆን አመልክተዋል።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 /የስድብና ማዋረድ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው በቀንና ሰዎች ባሉበት በመሆኑ፤ እንዲሁም የስድብ ድርጊቱን ከባድ ነው የሚያስብል ነገር ባለመኖሩ የወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 615 የሚያስቀጣው ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል ተብሎ የተደነገገ ስለሆነ ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች ፍ/ቤቱ በቅድሚያ አንዱን መምረጥ ስላለበት ፍ/ቤቱ በእስራት ከመቅጣት በገንዘብ መቀጮ መቅጣት አግባብ ነው ብሎ ስለመነበት ተከሳሽ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል።

ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ከወሰነ ደግሞ በመመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት የሚወሰን ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 የገንዘብ መቀጮው ከብር አስር እስከ ሦስት መቶ ብር ስለሆነና የወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ በመሆኑ መነሻ ቅጣቱ ከጣሪያው ብር ሦስት መቶ ብር በሁለት ሦስተኛ ዝቅ ብሎ ተሰልቶ ከሚገኘው ውጤት ጣሪያ ሳይበልጥ ይወሰናል። የብር ሦስት መቶ ሁለት ሦስተኛ ውጤት ብር አንድ መቶ ብር ስለሚሆን ቅጣቱ በመነሻው ብር አስር እና በዚህ አሁን በስሌቱ መሰረት በተገኘው ውጤት ብር አንድ መቶ ብር

መካከል ይወሰናል። ፍ/ቤቱም የተከሳሽ የወር ገቢን መሰረት በማድረግ ብር አንድ መቶ ብር እንዲሆን ተወስኗል። ይህን መነሻ ቅጣት ይዘን ወደ መመሪያው አባሪ 2 ስንሄድ ይህ የብር 100.00(አንድ መቶ ብር) የገንዘብ መቀጮ በአባሪ 2 እርከን 1 ስር የሚወድቅ በመሆኑ፤ የእርከን 1 ፈቃደ ስልጣን ደግሞ እስከ ብር አንድ ሺህ ድረስ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚሁ ፍቅድ ስልጣን መሰረት ብር 300.(ሦስት መቶ ብር) እንዲቀጡ ተወስኗል።

በወ/ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ያቀረበ ቢሆንም በዚህ በጠቅላላ ማክበጃ ምክንያት ከጣሪያው ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) ሊበልጥ ስለማይችል ፍ/ቤቱ ቅጣቱን አላከበደውም። በተከሳሽም በኩል በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስላልቀረበ ፍ/ቤቱ ከላይ የወሰነውን መጠን ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) ን ተከሳሽ በመቀጮነት እንዲከፍሉ ወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ በዚህ መዝገብ ለዋስትና ያስያዙት ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር)

ለቅጣቱ ዓላማ እንዲውል ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።